# የፍራንክፈርት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን

ከሁሉ አስቀድመን በአምላካችን በልዑል እግዚአብሔር ስም በጀርመን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኮለኝ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አባላት እንኳን ለ፴ኛው ዓመት የምሥረታ በዓል አደረሳችሁ እያልን፤ በተለይ ሊቀ ካህናት ዶ/ር መርዓዊ ተበጀን የደከሙበትንና የለፉበትን ውጤት ለማየት በመብቃተዎ እንኳን ደስ አለዎት እያልን፤ ፴፭ተኛውን የብር ኢዩቤልዩ እንዲሁ ለማክበር እንዲያበቃዎ ልባዊ ምኞታችንን እንገልጻለን።

በባዕድ ሀገር እንደ ቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ ሁሉ ነገር ተሟልቶ መንፈሳዊ አገልግሎት ለመስጠት የማይቻልበትና ብዙ ውጣ ውረድ የሚያስከትል ቢሆንም ለልዑል እግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ባለመኖሩ፤ በጀርመን ሀገር ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዷና ማዕከለ አውሮፓ በሆነው በፍራንክፈርት ከተማ የተቋቋመችው የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው ብዙ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቷን ለምእመናን በማበርከት ላይ ትገኛለች።

የልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ቤተ ክርስቲያኗ በብዙ ጥረትና ድካም ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንዲሆን የተገኘው ቤተ ክርስቲያን እጅግ ሰፊና በማንኛውም ነገር የተሟላ በመሆኑ ምእመናን ሳይጣበቡና ሳይቸገሩ ሥርዓተ ቅዳሴና ትምህርተ ወንጌል በሚገባ ተከታትለው፤ በረከተ እግዚአብሔርን አግኝተው፤ ከቅዳሴ ውጭ አረፍ ብለው፤ የሰንበት መክፈልትና በየወሩም የእመቤታችን የቅድስት ማርያምን የጽዋ ማኅበር ቀምሰው፤ ቡራኬ ተቀብለው እንዲሄዱ ዕድሉ ገጥሟቸዋል።



በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ በሰበካ ጉባኤ አባልነት ተመዝግበው የሚገኙ ሁለት መቶ ሃያ ስድስት ሲሆኑ፤ የአባልነት ግዴታቸውን የተወጡ ደግሞ መቶ ሃያ አንድ ናቸው።

በፍራንክፈርት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ አገልግሎቶች የሚሰጡ ሲሆን፤ ዘወትር በየሳምንቱ እሑድ ከንጋቱ ፩ ሰዓት ጀምሮ ሥርዓተ ቅዳሴና ስብከተ ወንጌል ይሰጣል። አስፈላጊው መንፈሳዊ አገልግሎትም ሁሉ ይከናወናል። በወር አንድ ጊዜም በካስል ከተማ መንፈሳዊ አገልግሎት ይሰጣል። የሰበካ ጉባኤው ምእመናን ለቤተ ክርስቲያን የሚገባውን አሥራት በኩራት እንዲያዋጡ የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ ነው። ምእመናን የሰበካ ጉባኤ አባልነት ክፍያ በባንክ ቤት በኩል እንዲያስተላልፉ ጥረት እያደረገ ሲሆን፤ በተጨማሪም በየሳምንቱ እሑድ ከቅዳሴ በኋላ ምእመናንን በአገልግሎት ያስተናግዳል።

ቤተ ክርስቲያናችን ምእመናኑን በማስተባበር ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት ለደረሰው ረሀብ ለወገኖቻችን እርዳታ ስድስት ሺህ ማርክ በመላክ የበኩሏን አስተዋጽኦ አድርጋለች። በዚህም ዓመት ለተከሠተው ረሀብ እያንዳንዳችን የመተባበርና የመርዳት ወገናዊ፤ ክርስቲያናዊና ሰብአዊ ግዴታ ስለአለብን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የእርዳታ ጥሪ ድምፅዋን በማሰማት ላይ ትገኛለች። በተጨማሪም በተለያዩ ዓመታት በበዓላት ዕለት በሺህ የሚቆጠር ማርክ በማሰባሰብ ለአብነት መምህራን በአሉበት አካባቢ እርዳታ ተደርጓል። ቤተ ክርስቲያናችን በዚህ በ፲፱፻፺፰ ዓ. ም. ውስጥ ካከናወነቻቸው ዓበይት በዓላት ውስጥ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

፩ኛ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቀኖና ወስና፤ ዓበይት ብላ ልዩ ክብርና አገልግሎት ከምትሰጣቸው በዓላት መካከል አንዱ የመስቀል በዓል በመሆኑ ዕለተ ደመራን በደመቀና በአማረ ሁኔታ ለማክበር እንጨት ቆርጦ፤ ደመራ ደምሮና ችቦ አብርቶ ሙሉ ለሙሉ እንደ ሀገራችን ለማዘጋጀት አስቸጋሪ ቢሆንም፤ የሚመለከታቸውን ክፍሎች በማነጋገርና ለቦታውም ሆነ ለደመራ እንጨቱ በማስፈቀድ ልክ እንደ ሀገር ቤቱ ደመራው

ተደምሮ፣ ሥርዓተ ጸሎቱ ደርሶ፣ በዓሉን የሚመለከት ያሬዳዊ ዜማ ተመርቶ፣ ችቦው ሲቀጣጠል፣ ሁሉም ምእመን ልክ ከሀገሩ ሆኖ የሚያከብረው በመምሰሉ መዘምራኑም ሆኑ ምእመናኑ „እኔስ ሀገሬን መሰለኝ“ እያሉ ሲዘምሩ ከፍተኛ ደስታ ይታይ እንደነበር በቦታው የነበረ ሁሉ የዓይን ምስክር ነው። በተለይም ለበዓሉ ድምቀት ከሚሰጠው ዋናው ምክንያት በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት የመስቀል በዓል ከብዙኃን ማርያም በዓለ ንግሥ ጋር በአንድ ላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲከበር በመወሰኑ ነው።

፪ኛ/ በያዝነው ዓመት የእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት ሆኖልን የመስከረም ብዙኃን ማርያምን ክብረ በዓል ታቦተ ሕጉን በማውጣት እጅግ በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል። ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ማኅበረ ምእመናን የቤተ ክርስቲያኗን መንፈሳዊ ጥሪ አክብረው በመገኘት ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤትንና በረከትን ለማግኘት ችለዋል።

፫ኛ/ በጨለማ የኖረው ዓለም ብርሃን ያየበትን፣ ሰውና እግዚአብሔር የታረቁበትን ትልቁን የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ልደት በዕለተ ቀኑ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ. ም. በሺህ የሚቆጠር ማኅበረ ምእመናን በመገኘት፣ ሥርዓተ ማኅሌቱ በደመቀ ሁኔታ ከተሰጠ በኋላ ሥርዓተ ቅዳሴው ተፈጽሞ፣ በሰላም ሠርሆተ ሕዝብ ሆኗል።

፬ኛ/ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን በዓለ ዕረፍት ምክንያት በማድረግ በየዓመቱ እንደሚከበረው ሁሉ በዚህ ዓመትም ጥር ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ. ም. እንደተለመደው በርካታ ማኅበረ ምእመናን ከተለያዩ የጀርመን ከተማዎች በግልም ሆነ በቡድን ብዙ ኪሎ ሜትር አቋርጦ በመምጣት እጅግ በደመቀ ሁኔታ አክብረዋል። በወጣው መርሃ ግብር መሠረት ማኅሌቱና ሥርዓተ ቅዳሴው እንዳለቀ ታቦተ ሕጉ ወጥቶ በሰንበት ት/ቤት መዘምራን የተዘጋጀው ወረቡ ተሸብሽቦ፣ የዕለቱ ትምህርትም ተሰጥቶ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል።

፭ኛ/ የፍራንክፈርት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤት መዘምራን ቤተ ክርስቲያኗ በምታከብራቸው ዓበይት በዓላት የመዝምራን ልዩ ልብስ በመልበስና በዓሉን የሚመለከት ጣዕመ ዝማሬ በማሰማት ለበዓሉ የሚሰጡት ድምቀት ሳይታወስ የሚታለፍ አይደለም። እንዲሁም ከፍተኛ አባላት ያሉት የቅድስት ማርያም የጽዋ ማኅበር ለቤተ ክርስቲያኗ የሚሰጠው አገልግሎት ከምስጋና ጋር ሊጠቀስ የሚገባው ተቋም ነው።

በዚህ አጋጣሚ፣ በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመበትን ፳ኛ ዓመት ለማክበር ለአበቃን ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን እያልኩ፣ መጭውንም ጊዜ ባርኮና ቀድሶ፣ የሰላምንና፣ የፍቅርን የኅበረትንና የአድነትን፣ የሐዋርያዊነትን ሥራ የምናከናውንበት ዘመን እንዲያደርግልን፣ በፍራንክፈርት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ምእመናንና በራሴም ስም እመኛለሁ።

አባ ሲራክ ወልደ ሥላሴ
የፍራንክፈርት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ